ሞንጎመሪካዉንቲ
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

# ደንብ

**ተዛማጅ ግባቶች፡-** ISB-RA
**ኃላፊ ጽ/ቤት፡-** የአካደሚ ዋና ኃላፊ

## ከቤት የሚሰጥ ትምህርት

I. **ዓላማ**

ለአካባቢ ፐብሊክ ትምህርት ቤት ስርዓቶች የቁጥጥር መስፈርቶችን የሚያስቀምጡ፣ በቤት ውስጥ ትምህርትን ለመተግበር የሜሪላንድ ህጎችን ቅደም ተከተሎች/አሰራሮች ለመመስረት

II. **የበፊት መነሻ/አመጣጥ**

በሜሪላንድ ሕግ ስር ካልተገለጸ/ካልተደነገገ በስተቀር፣ ዕድሜው/ዋ 5 እና ከዛ በላይ የሆነ/ች እና ከ 18 ዓመት በታች የሆነ/ች ልጅ ህጋዊ የሆነ አሳዳጊነት ወይም እንክብካቤ ባለው/ባላት እና በሚቆጣጠር-በምትቆጣጠር ሰው በትምህርት ዓመቱ ውስጥ አብዛኛዉን ጊዜ በሕዝባዊ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተመሳሳይ እድሜ ላሉ ልጆች የሚሰጥ ትምህርት፣ ትምህርት ቤት ገብቶ/ታ መከታተል ወይም መደበኛ፣ የተሟላ ትምህርት ማግኘት አለበት/አለባት።

በሞንጎመሪ ካውንቲ በቤት የትምህርት ፕሮግራም ውስጥ የሚሳተፍ/የምትሳተፍ ተማሪ በትምህርት ዓመቱ ውስጥ ሁሌም በሕዝባዊ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተመሳሳይ እድሜ ላሉ ልጆች በሚሰጠዉ መልኩ፣ ቢያንስ በመደበኛነት፣ የተሟላ/ጠንካራ ትምህርት ማግኘቱን/ማግኘቷን የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ወይም ወኪል መወሰን ይገባቸዋል።

III. **ቅደም-ተከተሎች/ሥርአቶች**

A. ለወላጆች/ሞግዚቶች መረጃ/ኢንፎርሜሽን

የ MCPS ጽ/ቤት የአካደሚ ዋና ኃላፊ ለልጃቸው(ልጆቻቸው) የቤት ውስጥ ትምህርት ለመስጠት ፍላጎት ላላቸዉ ለማንኛውም ወላጅ/ሞግዚት የመረጃ ማቴሪያሎችን/ቁሳቁሶችን ያቀርባል/ታቀርባለች። እነዚህ ማቴሪያሎች/ቁሳቁሶች ለ MCPS የቤት ዉስጥ ትምህርት ተቆጣጣሪ/ተወካይ የመገናኛ ኢንፎርሜሽን/መረጃ፣ጠቃሚ/አግባብነት ያለዉ የሜሪላንድ ህጎችና ደንቦች፣ እንዲሁም በ MCPS የሚፈለጉ ቅጾችን ያጠቃልላል።

B. አስፈላጊ ማስታወቂያ እና የፈቃድ ስምምነት

1. የቤት ውስጥ ትምህርት መርሃግብር ከመጀመሩ ቢያንስ ከ 15 ቀናት በፊት፣ ወላጅ/ሞግዚት የ MCPS ቅጽ 270-34፣ የቤት ዉስጥ ትምህርት ማሳወቂያ(በሚስጢር የሚያዝ)፣ ለ MCPS የቤት ዉስጥ ትምህርት ተቆጣጣሪ/ተወካይ ማስገባት/ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ከዚህ በታች በክፍል III.D በተደነገገው መሠረት፣ የተሰጠዉን ትምህርት MCPS ለመቆጣጠር እና ለመገምገም እንዲችል ወላጅ/ሞግዚት መስማማት/መፍቀድ አለባቸው፣ ወይም ከዚህ በታች በክፍል III.C እንደተገለፀው በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ (MSDE) ስር በተመዘገበ ህዝባዊ ባልሆነ

ት/ቤት ወይም ተቋም ቁጥጥር እና ግምገማዉ መካሄዱን ወላጅ/ሞግዚት ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

2. ልጁ/ልጅቷ በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ (MSDE) ስር በተመዘገበ ህዝባዊ ባልሆነ ት/ቤት ወይም ተቋም ክትትል/ቁጥጥር ስር እስካልሆነ/ች ድረስ፣ ከዚያ በኋላ በየአመቱ፣ ወላጅ/ሞግዚት የቤት ውስጥ ትምህርት መቀጠሉን በጽሑፍ ለ MCPS ማረጋገጥ/መግለጽ አለባቸው። የ MCPS የቤት ዉስጥ ትምህርት ተቆጣጣሪ/ተወካይ MCPS ቅጽ 270-36 ን፣ የቤት ዉስጥ ትምህርት ለመቀጠል አመታዊ ማስታወቂያ፣የቤት ዉስጥ የትምህርት ፕሮግራማቸው በ MCPS ክትትል/ቁጥጥር ስር ላሉት ወላጆች/ ሞግዚቶች ሁሉ ይልካል/ትልካለች።

3. በትምህርት ዓመቱ ውስጥ በልጅ/ልጅቷ የቤት ውስጥ ትምህርት ፕሮግራም ሁኔታ ላይ ለውጥ ከተከሰተ፣ ወላጅ/ሞግዚት ለ MCPS የቤት ዉስጥ ትምህርት ተቆጣጣሪ/ተወካይ ወይም ለተመዘገበ ተቆጣጣሪ ትምህርት ቤት ወይም ተቋም ተወካይ በጽሑፍ ማሳወቅ አለባቸው።

4. ከዚህ በታች በክፍል III.E በተደነገገው መሠረት፣ ተማሪው/ዋ በሕዝብ ትምህርት ቤት ወይም ሕዝባዊ ባልሆነ ትምህርት ቤት የሚመዘገብበትን/የምትመዘገብበትን ሁኔታ አስመልክቶ ወላጅ/ምግዚት መስማማት አለባቸዉ።

5. በተጨማሪም MCPS የሚከተሉትን ለወላጆች/ሞግዚቶች ያሳውቃል፡-

   a) በመደበኛነት መርሐግብር ተይዞላቸዉ በ MCPS ዉስጥ አድምንስተር በሚደረጉ/በሚሰጡ ደረጃቸዉን የጠበቁ የምዘና ፕሮግራሞች ላይ ለመሳተፍ የተማሪው/ዋ የመምረጥ መብት።

   b) ከዚህ በታች በክፍል III.G እንደተገለፀው፣ ሌላ በተደጋጋሚ የሚጠየቅ መረጃ/ኢንፎርሜሽን፡-

C. የቤት ውስጥ ትምህርት በተመዘገበ ሕዝባዊ ባልሆነ ትምህርት ቤት ወይም ተቋም ቁጥጥር/ክትትል ስር

የ COMAR §13A.10.01.05 መስፈርቶችን በሚያሟሉ እና በ MSDE ስር በተመዘገቡ ሕዝባዊ ባልሆነ ትምህርት ቤት ወይም ተቋም ቁጥጥር/ክትትል ስር የቤት ውስጥ ትምህርት ፕሮግራም ወላጆች/አሳዳጊዎች ለልጃቸው እንዲሰጥ ሊያደርጉ ይችላሉ።

1. እንደሚፈለግ ከላይ እንደተገለፀው፣ የቤት ውስጥ ትምህርት መርሃ ግብር ከመጀመሩ ከ15 ቀናት በፊት ወላጅ/ሞግዚት ሁሉንም ቅጽ 270-34 ን ለ MCPS ማቅረብ አለባቸው። ከዚህ በላይ እንደተገለፀው በተመዘገበ ሕዝባዊ ባልሆነ ትምህርት ቤት ወይም ተቋም ቁጥጥር ስር ያለ/ች ልጅ፣ ከታች በክፍል III.D የተመለከቱት መስፈርቶች አይመለከታቸዉም።

2. ክትትል/ቁጥጥር የሚያደርግ የተመዘገበ ሕዝባዊ ያልሆነ ትምህርት ቤት ወይም ተቋም ማድረግ ያለበት–

   a) በክትትላቸዉ/ቁጥጥራቸዉ ስር የቤት ዉስጥ ትምህርታቸዉ የሚቀጥል ተማሪዎችን መታወቂያ ከ MCPS ጋር ማረጋገጥ፤

   b) ወደ ክትትላቸዉ/ቁጥጥራቸዉ ስር የተጨመሩ ተማሪዎችን መታወቂያ ለ MCPS ማሳወቅ፤ እና

   c) ከእንግዲህ በኋላ በክትትላቸዉ/ቁጥጥራቸዉ ስር የሌሉ ተማሪዎችን መታወቂያ፣ ወይም

በትምህርት አመቱ ዉስጥ የቤት ውስጥ ትምህርታቸዉን በሚከታተሉት ተማሪዎች ሁኔታ ላይ ለውጥ ከተከሰተ ለ MCPS ማሳወቅ።

D. በ MCPS ቁጥጥር/ክትትል ስር ላሉ ልጆች የፖርትፎሊዮ ግምገማ

1. በ MCPS ቁጥጥር ስር የቤት ዉስጥት ትምህርት የሚወስዱ ልጆች ወላጅ/ሞግዚት፣ የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ተወካይ የትምህርት ማቴሪያሎችን/ቁሳቁሶችን ፖርትፎሊዮ እንዲገመግሙ፣ እና በሜሪላንድ ሕግ መሠረት ልጆች መደበኛ፣ እና የተሟላ ትምህርት ማግኘታቸዉን ለማረጋገጥ በትምህርቱ መርሃ ግብር ላይ ለመወያየት እንዲችሉ መፍቀድ አለባቸዉ።

   a) መደበኛ እና የተሟላ ትምህርት እየተሰጠ መሆኑን የሚያሳይ የማቴሪያሎችን ፖርትፎሊዮ ወላጅ/ሞግዚት ይይዛሉ።

   b) ግምገማው እና/ወይም ውይይቱ የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ተወካይ እና ወላጅ/ሞግዚት በጋራ በመስማማት በሚመርጡት ጊዜ እና ቦታ ላይ ይካሄዳል።

   c) በትምህርት ዓመቱ ውስጥ ቢበዛ ሦስት እንደዚህ ያሉ ግምገማዎች ይኖራሉ።

2. ተቀባይነት እንዳለዉ እንዲታሰብ፣ ወላጅ/ሞግዚት በእንግሊዝኛ፣ በሂሳብ፣ በሳይንስ፣ በማኅበራዊ ጥናቶች፣ በሥነ ጥበብ፣ በሙዚቃ፣ በጤና፣ እና የሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርት በሙሉ በትምህርት ዓመቱ ውስጥ መደበኛ የሆነ የተሟላ ትምህርት እንደሰጡ እና እንደ መማሪያ ቁሳቁሶች፣ የንባብ ቁሳቁሶች፣ እና የተማሪ የጽሑፎች ናሙናዎች፣ ዎርክሺቶች፣የሥራ ደብተሮች፣ የፈጠራ ቁሳቁሶችን የመሳሰሉ እለታዊ እና አግባብነት ያላቸዉ ማቴሪያሎች፣ እና በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ግምገማዎችን ያካተቱ ስለመሆናቸዉ ፖርትፎሊዮዉ ሊያሳይ ይገባል።

3. ልጃቸዉ የተመዘገበባቸውን/ቻባቸዉን ትምህርቶች ዕውቅና ከተሰጠዉ ወይም ካልተሰጠዉ ኮሌጅ የእያንዳንዱን ሴሚስተር ማጠቃለያ የሪፖርት ካርድ ወይም ትራንስክሪፕት ቅጂ ስለ ትምህርት ቁሳቁስ ፖርትፎሊዮ ለ MCPS ለማቅረብ ወላጅ/ሞግዚት መምረጥ ይችላሉ።

4. ሪፖርት፦ የቤት ዉስጥ ትምህርት ፕሮግራም ግምገማ የሚከናወነዉ በ MCPS ቅጽ 270-35 ነዉ፣ የቤት ዉስጥ ትምህርት ግምገማ፣ በትምህርት ዓመቱ ውስጥ ሁሌም በሕዝባዊ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተመሳሳይ እድሜ ላሉ ልጆች በሚሰጠዉ መልኩ፣ አግባብ ያለዉ ማቴሪያል በመጠቀም ቢያንስ በመደበኛነት፣ የተሟላ/ጠንካራ ትምህርት ማግኘቱን/ማግኘቷን በት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ወኪል ተከናዉኖ ከእያንዳንዱ ግምገማ በኋላ ለ MCPS የቤት ዉስጥ ትምህርት ሱፐርቫይዘር/ተወካይ ይቀርባል።

5. የ MCPS የቤት ዉስጥ ትምህርት ተቆጣጣሪ/ተወካይ ከወላጅ/ሞግዚት ጋር የፖርትፎሊዮ ግምገማ እና ዉይይትን አስመልክቶ ከሜሪላንድ ሕግ ጋር በሚጣጣም መልኩ መደበኛ፣ እና የተሟላ የትምህርት ፕሮግራም ተማሪው/ዋ ያለማግኘቱን/ያለማግኘቷን ከወሰነ/ች፣ የ MCPS የቤት ዉስጥ ትምህርት ተቆጣጣሪ/ተወካይ በፕሮግራሙ ውስጥ ያሉትን ጉድለቶች ሁሉ ለወላጅ ሞግዚት በጽሑፍ ያቀርባል/ታቀርባለች።

6. ስለማንኛውም ጉድለቶች በጽሑፍ ማስታወቂያ በደረሳቸው በ 30 ቀናት ውስጥ፣ ወላጅ/ሞግዚት ጉድለቱ እንደተስተካከለ ወይም እየተስተካከለ ስለመሆኑ ለ MCPS የቤት ዉስጥ ትምህርት ተቆጣጣሪ/ተወካይ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸዉ።

7. በቤት ውስጥ የትምህርት መርሃ ግብር ውስጥ ያሉ ተማሪዎች 18 ዓመት ከሆናቸው በኋላ፣ በዚህ ደንብ መሠረት የቤት ዉስጥ ትምህርት ፕሮግራማቸውን መገምገም አስፈላጊ አይሆንም።

E. በቤት ዉስጥ የትምህርት አሰጣጥን ማቋረጥ

1. በወላጅ/ሞግዚት በተወሰነዉ መሰረት

አንድ ወላጅ/ሞግዚት በትምህርት ዓመቱ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ለ MCPS የቤት ዉስጥ ትምህርት ተቆጣጣሪ/ተወካይ በማስታወቅ የቤት ዉስጥ ትምህርትን ማቆም ይችላል/ትችላለች። በ COMAR 13A.09.09.02B (4-9) እንደተገለፀው ተማሪው/ዋ በፍጥነት በተፈቀደ የህዝብ ወይም ህዝባዊ ባልሆነ ትምህርት ቤት መመዝገብ አለበት/አለባት።

2. በ MCPS በተወሰነዉ መሰረት

የ MCPS የቤት ዉስጥ ትምህርት ተቆጣጣሪ/ተወካይ አንድ ጉድለት ለማረም አጥጋቢ ዕቅድ አለመኖሩን ወይም ጉድለቱ እንዳልተስተካከለ ከወሰነ/ች፣ ወይም ወላጅ/ሞግዚት የትምህርት ቤት ሱፐርኢንተንደንት ተወካይ አስፈላጊዎቹን ግምገማዎች እንዲያካሂዱ የማይፈቅዱ ከሆነ፣ በ COMAR 13A.09.09.02B (4-9) እንደተገለፀው ተማሪው/ዋ በፍጥነት በተፈቀደ የህዝብ ወይም ህዝባዊ ባልሆነ ትምህርት ቤት በወላጅ/ሞግዚት አማካይነት መመዝገብ አለበት/አለባት።

3. በ MCPS ምደባ

ከተጠየቀ፣ የትምህርት ቤት ርዕሰመምህር/ተወካይ ከ MCPS የቤት ዉስጥ ትምህርት ተቆጣጣሪ/ተወካይ ድጋፍ ጋር፣ ለአዲሱ/ሷ ተመዝጋቢ ተገቢ የክፍል ደረጃ አመዳደብን ይወስናል/ትወስናለች።

a) ምደባው ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ከሆነ፣ ለምረቃ የሚሰጡ የክሬዲት ኮርሶች፣ ካሉ፣ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር/ተወካይ ይወስናል/ትወስናለች።

b) አግባብነት ካለዉ፣ እና በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር/ተወካይ በሚወሰነዉ መሠረት፣ ለተገቢ ምደባ እና ስለ ክሬዲቶች ለመወሰን ከተማሪው ጋር አግባብነት ያላቸው ግምገማዎች እና ቃለ-መጠይቆችን የማከናወን ስራ በተግባር ሊውል ይችላል።

F. ደረጃውን በጠበቀ ምዘና ላይ በፈቃደኝነት መሳተፍ

1. በ MCPS ቅጽ 270-34 ላይ ወላጅ/ሞግዚት የሚያመለክቱት፣ የቤት ዉስጥ ትምህርት ማስታወቂያ (በሚስጢር የሚያዝ)፣ ልጃቸው ደረጃውን በጠበቀ ምዘና/ፈተና ላይ እንደሚሳተፍ/እንደምትሳተፍ፣ በካውንቲ አቀፍ የፈተናዎች ቀን ዝርዝር ይሰጣቸዋል። ከዚያም ወላጅ/ሞግዚት የተወሰነ የፈተና ጣቢያ መረጃ ለማግኘት የት/ቤቱን ርዕሰ መምህር/ተወካይ ማግኘት አለባቸዉ።

2. የፈተና ውጤቶች በጋራ ኃላፊነት ጽ/ቤት /Office of Shared Accountability ሠራተኛ፣ በ MCPS የተማሪ ፋይል ላይ ከሚቀመጥ ቅጂ ጋር፣ በቀጥታ ለወላጅ/ሞግዚት ይላካል/ይመለሳል።

G. ዲፕሎማዎች፣ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች፣ የ MCPS ሥርዓተ ትምህርት፣ እና የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ግምገማዎች

1. በቤት ዉስጥ ከሚሰጥ የትምህርት መርሃግብር/ፕሮግራም፣ ወደ MCPS በዝዉዉር የተመዘገበ/ች፣ እና ሁሉንም የ MCPS የምረቃ መስፈርቶችን የሚያሟላ/የምታሟላ ተማሪ የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ መቀበል ይችላል/ትችላለች። የ MCPS የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የምረቃ መስፈርቶች በ MCPS ደንብ ውስጥ ይገኛሉ ISB-RA፣የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የምረቃ መስፈርቶች።

2. የቤት ውስጥ ትምህርት የሚቀበል/የምትቀበል ተማሪ በ MCPS የሁለተኛ ደረጃ አትሌቲክስ ወይም ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ አይችልም/አትችልም። ህዝባዊ ባልሆኑ ት/ቤቶች ፈቃድ ላይ ተመስርቶ፣ በቤት ዉስጥ ትምህርት ለሚቀበሉ ተማሪዎች ህዝባዊ ባልሆኑ ት/ቤቶች በአትሌቲክስ መርሃ ግብር እንዲሳተፉ፣ የሜሪላንድ የህዝብ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች አትሌቲክስ ማህበር ውስን ልዩ ሁኔታዎችን ይፈቅዳል።

3. የ MCPS ሥርዓተ ትምህርት እና ሌሎች የ MCPS የመማሪያ ቁሳቁሶች በቤት ዉስጥ ትምህርት ፕሮግራሞች ስራ ላይ እንዲዉሉ አይሰራጩም።

4. በፌዴራል የአካል ጉዳተኞች ግለሰቦች የትምህርት ሕግ መሠረት እንደ "Child Find" ሂደት አካል ሆኖ ለልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ብቁ መሆን አለመሆንን ለመወሰን የቤት ዉስጥ ትምህርት የሚቀበል/የምትቀበል ተማሪ ወላጅ/ሞግዚት ተማሪው/ዋ እንዲገመገም MCPSን የመጠየቅ መብት አላቸዉ።

H. ሪከርድ አያያዝ

የ MCPS የቤት ዉስጥ ትምህርት ተቆጣጣሪ/ተወካይ የሚከተሉትን ቁሳቁሶች ጨምሮ፣ ግን በዚህ ሳይገደብ፣ በቤት ዉስጥ ትምህርትላይ የሚሳተፉ የተማሪዎችን ፋይሎች ይጠብቃል/ትጠብቃለች፦

1. MCPS ቅጽ 270-34፣ የቤት ዉስጥ ትምህርት ማስታወቂያ(በሚስጢር የሚጠበቅ)

2. ደረጃውን የጠበቀ የ MCPS ወይም የስቴት የፈተና ውጤቶች እንደተገኘ/ተገቢ

3. MCPS ቅጽ 270-35፣ የቤት ዉስጥ ትምህርት ፕሮግራም ግምገማ፣ፕሮግራማቸው በ MCPS ቁጥጥር ለሚደረግላቸው ተማሪዎች

4. MCPS ቅጽ 270-36፣ የቤት ውስጥ ትምህርትን ለመቀጠል አመታዊ ማስታወቂያ (በሚስጢር የሚጠበቅ)፣ አግባብነት ካለዉ

5. ሁሉም ደብዳቤዎች እና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶች

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** Annotated Code of Maryland, Education Article, §7-301; Code of Maryland Regulations (COMAR) §13A.10.01.01 et seq; §13A.09.09.02B (4-9)

**የደንቡ ታሪክ፦**አዲስ ደንብ፣ ፌብሪዋሪ 1986፤ ተከለሰ ዲሰምበር 14/1987፤ ተከለሰ ጁላይ 1/1995፤ ተከለሰ ጁን 29/2005፤ ተከለሰ ጁን 29/2017፤ ተከለሰ ሰፕተምበር 5/2019።